EARLY CHILDHOOD EDUCATOR
PAY EQUITY FUND

# ለቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች የበጀት አመት 2024 (FY24) ምናባዊ መረጃ

ኦገስት 2023

OSSE

WE ARE WASHINGTON DC
GOVERNMENT OF THE
DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# ወደ ቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች እንኳን ደህና መጡ!



EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND

OSSE

WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

# የዙም ተሳትፎ

ጥያቄዎችዎን የ Q&A feature (**የጥያቄና መልስ ምርጫን**) በመጠቀም ያስገቡ።

ቀድመው መውጣት ይፈልጋሉ? በማንኛውም ጊዜ **ከስብሰባ ይውጡ** የሚለውን አዝራርን ይጫኑ።




ወደ **መገልገያ ጽሁፎች** የሚወስዱ ተጨማሪ **መረጃዎች** እና **ማስፈንጠሪያዎች** እዚህ ይጋራሉ።

ምርጫዎ በሆነ ቋንቋ ስብሰባውን ያዳምጡ። **የአማርኛ** ወይም **የስፓኒሽ አስተርጓሚን** ለማግኘት እዚህ ይጫኑ።

# በቀጥታ የሚተላለፉ ጥያቄዎች እና መልሶች







ጥያቄዎን እዚህ ይጻፉ እና ያስገቡ የምለውን ይጫኑ።

# የዛሬ ተናጋሪዎች ጋር ተዋወቁ

- **Sara Mead**፤ የቅድመ ትምህርት ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ፣ ኦፊስ ኦፍ ዚ ስቴት ሱፐርኢንተንደንት ኦፍ ኤጁኬሽን
- **Tierra Washington**፤ የፕሮግራም አስተዳዳሪ፣ ቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ





# አጀንዳ

1. የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊነት የገንዘብ ድጋፍ አጭር መግለጫ
2. የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ በጀት አመት 2024 (FY24) እንዴት እንደሚሰራ
2. Q&A
3. መዝጊያ እና ቀጣይ ደረጃዎች

# የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊነት የገንዘብ ድጋፍ አጭር መግለጫ

# የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊነት የገንዘብ ድጋፍ ምንድን ነው?

- የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊነት የገንዘብ ድጋፍ የልጅ እድገት ተቋም ሰራተኞችን ካሳ ለመጨመር ጥቅም ላይ የሚውል የኮሎምቢያ ዲስትሪክት መንግስት ልዩ የገንዘብ ድጋፍ ነው።
- ፕሮግራሙ የሚተዳደረው በOSSE ነው።

# FY22 እና FY23

- በFY22 እና FY23፣ OSSE ተጨማሪ ክፍያዎችን ለቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች ለመስጠት ከAidKit ጋር በመተባበር ሰርቷል።



# በቁጥሮቹ

| FY22 | FY23 (Q1-Q3) |
| --- | --- |
| **3,217** የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች ተጨማሪ ክፍያ አግኝተዋል | **3,854** የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች ተጨማሪ ክፍያ አግኝተዋል |
| **$38,372,000** ለቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች ተሰራጭቷል | **$31,147,500** ለቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች ተሰራጭቷል |

** ቁጥሮች ከኦገስት 16, 2023 ጀምሮ*

EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND

OSSE

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊነት የገንዘብ ድጋፍ እንዴት እንደሚሰራ

# በFY22 እና FY23፣ OSSE የክፍያ ፍትሃዊነት የገንዘብ ድጋፎችን በ Aidkit አማካኝነት ለቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች አከፋፍሏል።

- ከAidkit የሚሰጠው የመጨረሻው ክፍያ በሴፕቴምበር 2023 ይሰራጫል።



# ከ FY24 ጀምሮ፣ የክፍያ ፍትሃዊነት የገንዘብ ድጋፎች በልጅ እንክብካቤ አሰሪዎች አማካኝነት የሚሰራጭ ይሆናል።



# በFY24 ለቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች የሚደረጉ ቁልፍ ለውጦች

| FY22 እና FY23 | FY24 |
| --- | --- |
| አስተማሪዎች የገንዘብ ድጋፎችን ከAidKit ይቀበላሉ | አስተማሪዎች የገንዘብ ድጋፎችን ከአሰሪው ይቀበላሉ |
| ብቁ በሆኑ የሰራተኞች አይነቶች ያሉ ሁሉም አስተማሪዎች ለገንዘብ ድጋፎች ማመልከት ይችላሉ | ሰራተኞቹ የገንዘብ ድጋፎችን እንዲያገኙ ቀጣሪው መርጦ መግባት አለበት። |
| ተጨማሪ ክፍያዎች በACH ወይም አስቀድሞ በተከፈለ የብድር ካርድ | የደመወዝ/የክፍያ ጭማሪ ከአሰሪ መደበኛ የደመወዝ ክፍያ ጋር ተካትቷል። |
| የክፍያ መጠን በሰራተኛው አይነት ላይ የተመሰረተ ነው | ዝቅተኛ ደመወዝ በሰራተኛ አይነት **እና** በከፍተኛ የትምህርት ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ነው |

# ቁልፍ ቃላት እና ፍቺዎች

- **ዝቅተኛ ደመወዞች፦** አንድ የልጅ እድገት ተቋም በሰራተኞቻቸው አይነት እና የትምህርት ማስረጃዎች ላይ በመመስረት ለመሪ መምህራንን እና ለረዳት መምህራንን የሚከፍለው ደመወዝ/ክፍያ
- **መደበኛ የደመወዝ ክፍያ፦** በአሰሪዎ በመደበኛነት ክፍያ የሚያገኙበት ዘዴ
- **የሰራተኛ አይነት፦** በስራ የሚጠሩበት የስራ ድርሻ ምንም ይሁን ምን በቅድመ ትምህርት ፈቃድ መስጫ መሳሪያ ክፍል (DELLT) (ለምሳሌ፣ መምህር፣ ረዳት መምህር፣ የቤት ውስጥ ተንከባካቢ፣ ወዘተ) ውስጥ ያለዎት ሚና
- **ከፍተኛው የትምህርት ማስረጃ፦** የያዙት ከፍተኛ ዲግሪ ወይም የትምህርት ማስረጃ (ለምሳሌ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ፣ የልጅ እድገት ተባባሪ[CDA]፣ በቅድመ ልጅነት ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ [ECE]፣ ወዘተ) በDELLT ተመዝግቧል

# በFY24 የክፍያ ፍትሃዊነት የገንዘብ ድጋፎችን ለመቀበል፣ ቀጣሪዎ መርጦ መግባት አለበት

- በFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊነት የገንዘብ ድጋፍ ለመሳተፍ መርጠው የገቡ ተቋማት ለሰራተኞች ከፍተኛ ደመወዝ ለመክፈል ከOSSE የገንዘብ ድጋፎችን ያገኛሉ።
- ይህ ከቀድሞዎቹ አመታት የተለየ ሲሆን፣ በብቁ የሰራተኞች አይነቶች በOSSE-ፈቃድ ባላቸው ተቋማት የተቀጠሩ ሁሉም የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች ለገንዘብ ድጋፎች ማመልከት ይችላሉ።
- የልጅ እድገት ተቋማት በቅድመ ልጅነት ትምህርት ሰጪ ክፍያ ፍትሃዊነት ፈንድ ውስጥ ለመሳተፍ አይገደዱም፣ ነገር ግን በጣም የሚበረታታ ነው።
- **በFY24 ለመሳተፍ አቅደው እንደሆን ቀጣሪዎን ይጠይቁ!**

# አሰሪዬ ለመሳተፍ ከመረጠ ለእኔ ምን ማለት ነው?

- **በፕሮግራሙ ውስጥ በሚሳተፍ ተቋም ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ከሆነ፣** አሰሪዎ ብቁ ለሆኑ ሰራተኞች ቢያንስ የFY24 ዝቅተኛ ደመወዞችን መክፈል ይጠበቅበታል።
- ብቁ በሆነ የሰራተኛ አይነት ከተቀጠሩ ተሳታፊ አሰሪዎች የገንዘብ ድጋፎችን በመደበኛ የደመወዝ ክፍያዎ ውስጥ ይጨምራሉ።
- አሰሪዎች የመጀመሪያ ሩብ አመት የልጅ እድገት ተቋም (CDF) የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት ክፍያ እስኪያገኙ ድረስ ብቁ ለሆኑ ሰራተኞች የFY24 ዝቅተኛ ደመወዞች እንዲከፍሉ አይገደዱም።
  - መርጦ የመግባቱን ሂደት እስከ ሴፕቴምበር 30፣ 2023 ድረስ ላጠናቀቁ አቅራቢዎች የመጀመሪያው ሩብ አመት ክፍያ በዲሴምበር 2023 ይሰራጫል።
  - ቀጣሪዎ ለመሳተፍ ከመረጠ፣ ቀጣሪዎ የመጀመሪያ ክፍያውን ከተቀበሉ በኋላ በደመወዝ ክፍያዎ ላይ የተንጸባረቀውን ማየት አለብዎት።

# አሰሪዬ ላለመሳተፍ ቢመርጥስ?

- **በፕሮግራሙ ውስጥ በማይሳተፍ ተቋም ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ከሆነ፣** አሰሪዎ ከቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ምንም አይነት የገንዘብ ድጋፎችን አይቀበልም እንዲሁም ለሰራተኞች የ FY24 ዝቅተኛውን ደመወዞች እንዲከፍል አይገደድም።
- አሰሪዎች በማንኛውም ጊዜ ወደ ቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ መርጠው ለመግባት መምረጥ እና የሚቀጥትውን የሩብ አመት ክፍያ መቀበል ይችላሉ።
- ሁሉም ቀጣሪዎች የ2016 የፍትሃዊ እድል ዝቅተኛ ደመወዝ ህግ እንዲሁም በዲስትሪክቱ የልጅ እንክብካቤ ድጎማ ፕሮግራም ላይ ለሚሳተፉ የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች፣ የ2006 የኑሮ ደሞዝ ህግን ጨምሮ **በሁሉም ቀጣሪዎች ተግባራዊ የሚሆኑትን የሰራተኛ ደመወዝ እና ሰአቶችን በተመለከተ ሌሎች የዲስትሪክት እና/ወይም የፌደራል ህጎችን እና መስፈርቶችን ማክበር አለባቸው።**

# የገንዘብ ድጋፎችን ለመቀበል ብቁ የሆኑት ምን አይነት የሰራተኛ አይነቶች ናቸው?

- ከOSSE የገንዘብ ድጋፎችን የሚያገኙ የልጅ እድገት ተቋማት ብቁ ለሆኑ መሪ መምህራን እና ረዳት አስተማሪዎች በDELLT ውስጥ በሚከተሉት የሰራተኛ አይነቶች፣ ዝቅተኛውን ደመወዝ የሚያሟሉ ወይም ከዚያ የሚበልጡ ደመወዞችን መክፈል አለባቸው።

| በDELLT ውስጥ የሚከተሉት የሰራተኞች አይነቶች እንደ ***ረዳት መምህር*** ብቁ ይሆናሉ፡- | በDELLT ውስጥ የሚከተሉት የሰራተኞች አይነቶች እንደ ***መሪ መምህር*** ብቁ ይሆናሉ፡- |
| --- | --- |
| • ረዳት አስተማሪ<br>• ሞንቴሶሪ ረዳት መምህር<br>• የPre-K የማሻሻያ እና ማስፋፊያ ፕሮግራም (PKEEP) ረዳት መምህር<br>• ተባባሪ የቤት እንክብካቤ ሰጪዎች | • መምህር<br>• ሞንቴሶሪ መምህር<br>• የተስፋፋ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ<br>• የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪዎች |

- በDELLT ስለ እርስዎ የሰራተኛ አይነት እርግጠኛ ካልሆኑ፣ እባክዎን ከአሰሪዎ ጋር ይነጋገሩ።
- ተቋማት በሌላ ሚና ውስጥ ላሉት ሰራተኞች ካሳ ማስተካከል ይችላሉ፣ ነገር ግን አይገደዱም።

# የረዳት መምህር የFY24 ዝቅተኛ ደመወዞች ስንት ናቸው?

| **ረዳት አስተማሪ**<br>(ረዳት መምህር፣ ሞንቴሶሪ ረዳት መምህር፣ የPKEEP ረዳት መምህር እና ተባባሪ የቤት ውስጥ ተንከባካቢ) | | |
|---|---|---|
| **የትምህርት ማስረጃዎች** | **ለFY24 ዝቅተኛ ደመወዞች (አመታዊ ደመወዝ)** | **ለFY24 ዝቅተኛ ደመወዞች (የሰአት ደመወዝ)** |
| ከ CDA ያነሰ | $43,865 | $21.09/ሰዐት |
| CDA | $51,006 | $24.52/ሰአት |
| ተባባሪ ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ | $54,262 | $26.09/ሰአት |

- አሰሪዎች እነዚህ የስራ ድርሻዎች/የትምህርት ማስረጃዎች ላላቸው አንዳንድ ሰራተኞች የበለጠ ለመክፈል ሊመርጡ ይችላሉ፣ ነገር ግን ተሳታፊ ቀጣሪዎች ያነሰ ክፍያ ላይሰጧቸው ይችላሉ።
- የFY24 ዝቅተኛው ደመወዞች ለቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ግፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራም የተወሰኑ ናቸው። ከግዛት እና ከፌደራል ዝቅተኛ የደመወዝ መስፈርቶች ጋር አንድ አይነት አይደሉም።

# የዋና መምህሩ የFY24 ዝቅተኛ ደመወዞች ስንት ናቸው?

| መሪ መምህር<br>(መሪ መምህር፣ ሞንቴሶሪ መምህር፣ የተስፋፋ የቤት ውስጥ ተንከባካቢ እና የቤት ውስጥ ተንከባካቢ) | | |
|---|---|---|
| **የትምህርት ማስረጃዎች** | **ለFY24 ዝቅተኛ ደመወዞች (አመታዊ ደመወዝ)** | **ለFY24 ዝቅተኛ ደመወዞች (የሰአት ደመወዝ)** |
| CDA ወይም በECE ውስጥ ከ15 ሰአታት የሚበልጡ ወይም እኩል የሆኑ 48 ክሬዲት ሰአታት | $54,262 | $26.09/ሰአት |
| በECE ተባባሪ ዲግሪ ወይም በECE ውስጥ 24 ክሬዲት ሰአታት በላይ ወይም እኩል የሆነ ተባባሪ ዲግሪ | $63,838 | $30.69/ሰአት |
| በ ECE የመጀመሪያ ዲግሪ (ወይም ከዚያ በላይ) ወይም በECE የመጀመሪያ ዲግሪ (ወይም ከዚያ በላይ) ከ24 ክሬዲት ሰአታት በላይ ወይም እኩል የሆነ | $75,103 | $36.11/ሰአት |

- አሰሪዎች እነዚህ የስራ ድርሻዎች/የትምህርት ማስረጃዎች ላላቸው አንዳንድ ሰራተኞች የበለጠ ለመክፈል ሊመርጡ ይችላሉ፣ ነገር ግን ተሳታፊ ቀጣሪዎች ያነሰ ክፍያ ላይሰጧቸው ይችላሉ።
- የFY24 ዝቅተኛው ደመወዞች ለቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ግፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራም የተወሰኑ ናቸው። ከግዛት እና ከፌደራል ዝቅተኛ የደመወዝ መስፈርቶች ጋር አንድ አይነት አይደሉም።

# አሰሪዬ ምን ያህል የገንዘብ ድጋፍ ይቀበላል?

ብቁ የሆኑ አስተማሪዎች ብዛት፣ በሰራተኞች አይነት እና በትምህርት ማስረጃ

\+

በድጎማው ውስጥ የተመዘገቡ ልጆች መቶኛ

→

ጠቅላላ የሽልማት መጠን

OSSE
WE ARE WASHINGTON DC
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# Q&A

# የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች ለ FY24 እንዴት መዘጋጀት ይችላሉ?

- **ከአሰሪዎ ጋር ይነጋገሩ**
  - በ FY24 ቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ለመሳተፍ አቅደው እንደሆን ቀጣሪዎን ይጠይቁ።
- **የሰራተኛዎን አይነት ያረጋግጡ**
  - በDELLT ውስጥ ያሉት የቅድመ ልጅነት አስተማሪ የሰራተኛ አይነት በተቀጠሩበት ተቋም ባላቸው ሃላፊነቶች እና በብቃታቸው ላይ የተመሰረተ ነው። በ DELLT ውስጥ በእርስዎ የሰራተኛ አይነት ላይ እርግጠኛ ካልሆኑ፣ አሰሪዎን ይጠይቁ።
- **መረጃዎ የዘመነ መሆኑን ያረጋግጡ**
  - አዲስ የትምህርት ማስረጃ ያገኙት በቅርቡ ከሆነ፣ በDELLT ውስጥ እንዲሰቅሉት የትምህርት ማስረጃውን ለአሰሪዎ ማቅረብዎን ያረጋግጡ።

OSSE

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# የዛሬውን የመረጃ ክፍለ-ጊዜ ስለተካፈሉ እናመሰግናለን!

በ FY24 የቅድመ ልጅነት ትምህርት ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎን የሚከተለውን ይጎብኙ፡- osse.dc.gov/fy24ecepayequity

የመገልገያ ጽሁፎች፥

- ለቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

ጥያቄዎች?

- OSSE.ECEPayEquity@dc.gov